# ለአዲስ ሀገር አዲስ ልሳን

ዓለማየሁ ሞገስ 10-29-17

ጥናታዊ ፅሁፎችም ሆነ ያታላላቅ ሀገር መሪ ንግግሮች ባለፉት 30 አመታት በአፍሪካ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መብት እያደገ መምጣቱን ይጠቁማሉ። በእርግጥም ከ26 ዓመት ወዲህ በአገራችን ሀሳብን ያለማንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት የመግለፅ መብት ህገ-መንገስታዊ ዋስትና ተሰጥቶት እያደገ መጥቷል። የሀገራችን ህዝቦች ሀሳባቸውን ያለገደብ በነፃ የመግለፅ ህገ መንግስታዊ ዋስትና ተከትሎ በልዩ ልዩ የውጭም ሆነ የውስጥ ተፅዕኖ ምክንያት የሀገራችን ፕሬስ እንደሌሎች የአህጉሪቱ ሚዲያዎች ሁሉ ለሀገሪቱ ተህድሶ የድርሻውን ያህል እንዳያበረክት የሚያደርጉ መሰናክሎች ይስተዋሉበታል፤

ሀገሪቱ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመር መከተል ከጀመረች ጊዜ አንስቶ የሚንቀሳቀሱ የፕሬስ ውጤቶች (ጋዜጦች፤መፅሄቶች፤መፅሀፍት፤ኤሌክትሮኒክሶችን ጨምሮ ወዘተ....) የትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ምንጭ ሆኖ ከመስራት ይልቅ ስም የሚያጠፉ ፤ አሉባልታ የሚያራግቡ፤ ጸያፍ ወይም ስድ የሆኑ ጉዳቶችን ሲያሰራጩ ተስተውለዋል።

በአገራችን ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳብን በነፃ የመግለፅ ህገ -መንግስታዊ ዋስትና ባገኘበት ማግስት ፖለቲከኞች ህዝብን በፖሊሲያቸውና በፖለቲካ አቋማቸው የሚያማልል አጀንዳ ቀርፀው ወደ ራሳቸው መሳብና ማሳመን ሲሳናቸው፤ ተፎካካሪያቸውን መቆቋም ሲያቅታቸው የሚዲያ ተቋም ከፍተው ወይም ተጠግተው ሲፋለሙ ማየት የተለመደ ሆኖ ቆይቷል።

እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ውድድር በደሀ ሀገር ቀርቶ በሀብታሞች ዘንድም እጅግ የተወገዘና በሀብትና ህዝብ ህይወት ላይ እንደ መቀለድ ተደርጎ ይወሰዳል። የሙያው ስነ ምግባርም አይፈቅድም ሙያውን ማቆሸሽ፤ ማበላሸትና ከመገደል ይቆጠራል።

ህብረተሰቡ ለዘርፉ ሚሰጠው ክብርና የሚኖረው ዕምነትም የተዛባ ሆናል። ሙያተኞችም ለእንዲህ ዓይነቱ ሚዲያ አገልጋይ ከሆኑ ለሙያው ስነምግባረ ተገዥ አይሆኑም ።

ከጋዜጦችና መፅሄቶች ባሻገር የሚታተሙ አንዳንድ መፃህፍት ራሳቸውን ገዳይ፤ ራሳቸውን ተኳሽ፤ ራሳቸውን ቀጭ ፤ ወዘተ...አድርገው የሚያቀርቡበት ዕድል ገደብ አሁን ድረስ አልተበጀለትም። በዚህን ወቅት ህብረተሰቡ ሚዛናዊና ቅን መረጃ አግኝቶ የተሻለ ህይወት ለመምራት የሚያደርገውን ጥረት ሊያግዝ አይችልም።

የዘርፉ ምሁራን እንደሚመክሩት ጋዜጠኞች በኢኮኖሚ ጥቅማጥቅም ልዩ ፍላጎት የሚደለሉ ከሆነ ሙያው የህብረተሰብ ለውጥ መሳሪያ ሳይሆን የእንጅራ መፈለጊያ ተደርጎ ይወሰዳል።

በደቡብ አፍሪካ ርዕሰ-ከተማ በሆነችው ጆሀንስ በርግ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2016 የአህጉሪቷ መገናኛ ብዙሀን አመራሮች ፎረም ውይይት መድረክ ወቅት የተንፀባረቀው አስተያየትም ይህንኑ በአህጉሪቱ የሚስተዋለውን የተዛባ የመገኛኛ ብዙሀን አሰራር የሚያወግዝ ነበር።

ፎረሙ በነፃነት ዋዜማም ይሁን ማግስት የተቋቋሙት የአህጉሪቷ ሚዲያዎች የህዝቡን ጥቅም ሙሉ በሙሉ አሳልፈው ለባዕዳን በሚሰጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን አመልክቷል። የአፍሪካ ሚዲያዎች በተለይም የኢንግሊዝኛ ፕሮግራሞቻቸው አሁንም ከዚህ ችግር የተላቀቀ አለመሆኑን ጉባኤው አስምሮበታል።

የሚዲያዎች ኤዲቶሪያል ቅኝት እና የዜና መምረጫ እሴቶቻቸው መስፍርት የሀገሬውን ህዝብ ብሄራዊ ፍላጎትና ጥቅም ከማስጠበቅ ይልቅ በባህሪው ከአንድ አቅጣጫ የሚንቆረቆር/ Trickled Down/፤ ማህበራዊና ቁሳዊ መሻሻልን በዘላቂነት ማምጣትን ታሳቢ ያላደረገና የጋራ መግባባትን ያገለለ ነበር አሁንም በዚሁ ቀጥሏል ሲል ተችቷል።

በቀጣይ የአፍሪካ ሀገሮች የጋራ ዕቅድ 2063 ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ ፤አህጉሪቱ ስርነቀል የሆነ የሚዲያ ልማት ላይ ስራ መስራት የግድ መሆኑን በጉባኤው ማጠቃለያ የጋራ አቋም ተወስዷል።

ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ በኋላ አክትሞለታል ተብሎ የሞት ፍርድ የተበየነበት የልማታዊ መንግስት አስተሳሰብ አገግሞ በአዲስ ጉልበትና አዲስ አስተሳሰቦች ታጅቦ አዲስ ብስራትን ይዞ በአለማችን ብቅ ብሏል።

የብስራት ዘገባው የተናኘው አለማችን ከአንዱ ልዕለ -ሀይል ወደ በርካታ ልዕለ- ሀያላን አስተሳሰቦችና ህዝቦች ዓለም ሽግሽግ በምታደርግበት ወቅት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል። ሀገራችን ኢትዮጲያም ከዜሮ በሚጀምር ስር ነቀል የፖለቲካል ኢኮኖሚ መስመር በዓለማቀፋዊው የሽግግር ዘመን ብስራት ዋና ህዝብ ግንኙነት ሆና እያገለገለች ነው ብንል ማጋነን አይሆንም።

ኢትዮጲያ በልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመር አስተሳሰብ ለረጅም ዘመን ከነበረችበት ድህነትና ኋላ ቀርነት አላቆ በአጭር ጊዜ ወደ መካከለኛና ከዚያም ከፍተኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ጎራ መቀላቀል የሚያችል ጉዞ ጀምራለች። አዲሲቱ ኢትዮጲያ በአዲሱ የፖለቲካ ዕሴትና ባህል የምታስጎመጅ ሀገርና የዓለምን ቀልብ መሳብ የጀመረች ሀገር ነች።(IMF,WB,etc…) ሪፖርቶች በዋቢነት ይጠቀሳሉ።

ዓለማቀፋዊውን ክስተት ተከትሎ የሀገራችንን አዲሱን የልማትና ፖለቲካ ባህል ህዝባዊ መሰረት የሚያስይዝና አንደበት የሚሆን መገናኛ ብዙሀን ሊኖራት ግድ ይላል። ሀገሪቱ ከሀያ ዓመት ወዲህ የተጓዘችበትን የልማትና የዲሞክራሲ ጎዳና ያስመዘገበችውን ዕድገትና የሚያጋጥሙትን ተግዳሮቶችና ሊወሰዱ ስለሚገባቸው መፍትሄዎች ቅልብጭ አድርጎ ማሳየት የሚችል፤ ከውጭ ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ሚዲያ ያስፈልጋል።

በሀይል ሳይሆን በህዝቦች በጎ ፈቃድ ላይ ተንተርሳ የተፈጠረችዋን የአዲሷን ኢትዮጲያ ስርዓት ማቆም ፤መጭው ትውልድ የሚቀበላቸውን ዕሴቶች የፖለቲካ ልማዶች ተቋማትና የህግ ችካሎችን በዘላቂነት ማነፅ የሚችል ብዙሀን መገናኛ ያስፈልጋል። ከልዩነቶች ይልቅ በሚያስማሙ እሴቶች የታነፀ ትውልድ መፍጠር የሚችል ህዝብ ግንኙነት ይጠይቃል።

በድህነትና ኋላ ቀርነት ሁብረተሰቡ ይዟቸው የቆዩትን የተዛቡ ኢትዮጲያዊ ማንነትና ዕሴቶች ማስጣል የሚችል የሚዲያ ስራ እንደ ዋነኛ ግብ አድርጎ የሚሰራ የሚዲያ አመራር ያስፈልገናል።

ይሁን እንጅ፤ ሚዲያው ሁለንተናዊ ልማታችን የሚጠይቀውን የኢዲቶሪያል ስነ-ምግባርና ሙያዊ ብቃት ታንፆ በሀገር ግንባታ ላይ ማበርከት የሚገባውን ያህል እንዳያበረክት ከሚያደርጉ ወቅታዊ መሰናክሎች መካከል በዋናነት ሚዲያዎች አሰላለፍ ላይ ጥያቄ መነሳቱ አልቀረም።

ከቀዝቃዛው ጦርነት መብቂያ በኋላ የአገራችንንም ሆነ የአፍሪካን ህዝቦች እያወደ የሚገኘው የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመራው ልማታዊ ሚዲያ አንዱ ሲሆን ፤በሌላ በኩል ደግሞ በተለመደውና በአክራሪ የነፃ ገበያ መርህ የሚመራው የሊበራል ሚዲያ ሀይሎች አሰላለፍ ነው።

ሊበራል ሚዲያ አሰላለፍ በአገራችን በምትከተለው ስልተ-ምርት ወይም ሞድ ኦፍ ፕሮዳክሽን ከአጋጅነቱ ይልቅ የልማት ማነቆ በሆኑ መረጃዎችና አስተሳሰቦችን በማስረፅ ወይም በኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የሚፈረጅና በተግባርም የተመሰከረለት ነው።

በመሆኑም ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስታት የሚዲያ ልማት ስራን በልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመር የተቃኘና ኪራይ ሰብሳቢ አመለካከትን የሚገራ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ስራ መምራትን ቀጠሮ ሊሰጡት አይገባም የሚል የነፃ ሚዲያ ልማት ጅምር በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል ።

የሚዲያ ልማት ሲባል ከመሰረተ-ልማት ጀምሮ ሙያው በአመለካከት የበሰሉ አመራሮችና ፈፃሚዎችን ማፍራት ፤በገንዘብ አቅም ራሳቸውን የቻሉ የሚዲያ ተቋማትን ማጠናከር የአገራችንን ብሎም የአህጉሪቷን ህዳሴ ዕውን የሚያደርግ የሚዲያ ስነ-ምግባር ማዕቀፍ ማዘጋጀት ወሳኝ ስራ ተደርጎ ሊከናወን ይገባዋል የሚሉ ወገኖች ጥቂት አይደሉም።

ከሚዲያ መሰረተ-ልማት አኳያ ብሄራዊ ክልሎች መሰረታዊ የሚባል ዕርምጃ እየወሰዱ ይታያል። ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቀውን ሚዲያ ልማት ትኩረት ሰጥተው በማሟላት ረገድ የተጓዙበት ርቀት ፕሬስ ለዘላቂ ልማት፤ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት የበለፀገ ሀገርና ህዝብ ለመፍጠር ቁርጠኛ አቋም ተይዞ እየተሰራ ስለመሆኑ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ከቅደም ተከተል አኳያ ለፕሬስ ዕድገት የሚጠቅመው የህዝብ ተሳትፎ፤ የትክክለኛ መረጃ ምንጭ መሆን ነው። ተሳትፎ ሲባል ቀጣይነት ያለው፤ ከድግግሞሽ/ዲፕሊኬሽን/ የጸዳ፤ ግልፅ ፤የተቋማትን ስትራተጅክ ዓላማና ራዕይ ከመቅረፅ ጀምሮ በተገቢው መንገድ ለሚዲያ ማቅረብ ይጠይቃል።

ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ የማቅረብ ስራ ባለድርሻ አካላትና ሚዲያው ተቀራርቦ በመስራት የሚፈታ ችግር መሆን አለበት። ባለድርሻ አካላትና የሚዲያ ተቋማት ተቀራርበው ባልሰሩበት ሁኔታ ሚዲያ ለተደራሹ የትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም። የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ለሚዲያ ዕድገት ወሳኝ የሚሆነው ለሚዲያ ፈሰስ በሚያደርጉት ሀብት ብቻ አይደለም ። ባለድርሻ አካላት በስፖንሰርሽፕ፤ በማስታወቂያ፤ በስብስክሪፕሽን ከሚያፈሱት ሀብት ይልቅ ባለድርሻ አካላት ለሚዲያው በሚያቀርቡት ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ለሚዲያ እድገት አስተዋፅኦ አለው።

በአገራቀፍ ደረጃ የተደረገ ጥናት በመንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት ትልቁ የጋራ ችግር ጥራት ያለው የመረጃ አመራርና አጠቃቀም መዘርጋት አለመቻል ነው ይላል። ጥናቶች ጨምረው እንደሚያስረዱት ከፍተኛ የስራ ሀላፊዎች ስለተቋማቸው አጠቃላይ ስትራተጅም ሆነ አቅጣጫ ላይ ወጥና ከድግግሞሽ ነፃ የሆነ መረጃ የሌላቸው መሆኑ ጉዳዩን አሳሳቢ ያደርገዋል። ሁሉም የተቋም መረጃ የተከለከለና ምስጢራዊ አድርጎ መገንዘብ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ላይ አሉታዊ አስተዋፅኦ ማሳደሩን ጥናቱ ማመላከቱን የጥናቱ ባለቤት ጨምሮ አብራርቷል።

በዚህም ምክንያት የመንግስትም ይሁን የግል ሚዲያ ተቋማት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ተአማኒነትና ተፅዕኖ ፈጣሪ መልዕክት ለአድማጮቻቸው ይዘው ለመቅረብ መቸገራቸው አይቀርም። በተቋማትና የተቋማት ስትራተጅክ አጋር በሆነው ሚዲያ መካከል ያለው የግንኙነት መስመር መላላት መረጃዎችን ምስጢራዊና ውድ ያደርጋቸዋል።

የመረጃ አስተዳደርና አጠቃቀም ባልዘመነበት ሁኔታ ሚዲያ ህዝቡንም ተቆጣጣሪ አካሉንም የሚያረካ ይዘት ጨብጦ ሊወጣ አይችልም። መገናኛ ብዙሀን የወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ምንጭ ሆነው አድማጮቻቸውንም ሆነ ህግ አውጭውን የሚያረኩ አይሆኑም። የልማትና መልካም አስተዳደር በማስረጽ ህዝብን የስልጣን ባለቤት የማድረግ ተልዕኳቸውን ሳይወጡ ይቀረሉ። ይላሉ የዳይሜንሽን ኦፍ ሞደርን ጆርናሊዝም ደራሲ ( N.C Pant & G. Tender Kumar).

እነኚሁ የዘርፉ ምሁራን ያለምንም ጥርጥር በአስቸጋሪ ብሄራዊ አደጋ ወቅት ጋዜጦች በሚያትሟቸው ዜናዎችና ትንታኔዎች አደጋውን በሚያባብስ መንገድ እንዳይከተሉ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ይመክራሉ። የፕሬስ ‘’ ነፃነት’’ ማለት ያገኘውን ሁሉ ማተምና ማሰራጨት ፈቃድ ማግኘት ወይም መቀበል ፤ ወይም ከህዝብ ጥቅምና ከህግ በተቃራኒ መጓዝ ሳይሆን የህግ የበላይነትን ማክበርና ማስከበር ጭምር መሆኑን ጭምር በማስገንዘብ።

ሚዲያ የትክክለኛና ወቅታዊ መረጃ ምንጭ ከሆነ አድማጭ የመያዝ አላማውን ያሳካል። አድማጭ ያለው ፕረስ ደግሞ አገልግሎትና ምርታቸውን ለመሸጥ/ለማስተዋወቅ ወደ ሚዲያው የሚመጡ ደንበኞች ቁጥር ይጨምራል። በሚዲያው ለማስታወቂያ፤ ለስፖንሰርሽፕ በመሳሰሉት ገቢ የመሰብሰብ አቅሙ ይገነባል። ሚዲያስ ገቢው ባደገ ቁጥር ደግሞ ጠንካራ ባለሙያዎችን የመቅጠር አቅም ይኖረዋል። ሚዲያው የጠንካራ ባለሙያዎች ተቋም ይሆናል ማለት ነው ።

አሁን አለማቀፍ ዕውቅና በተቸራቸውና ዓለማቀፍ ታዋቂነት ያተረፉ ሚዲያዎችም ታሪክ የሚያሳየን ዕውነታ ይህንኑ ነው። ይህ ባልሆነበት የሚዲያዎች ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሆኑት የመንግስት ታላላቅ ተቋማት ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ለሚዲያዎች ማድስ ባልቻሉበት ሁኔታ ሚዲያዎች የህብረተሰቡን የመረጃ ጥማት ሊያረኩና ተደማጭ ሊሆኑ አይችሉም።

አንድ ሚዲያ ለአድማጮቹ ህይወት ቅርብ የሆነ ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ባለቀረበ ጊዜ የዘርፉ ባለሙያዎች ‘’ ለአድማጮች የሬዲ ወይም ቴሌብዥናቸውን ቁልፍ በጣታቸው አንዴ ብቻ ከመጫን የከበደ ስራ የለም ! ! ’’ ይላሉ።

ልማታዊ ሚዲያ የህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፤ ከድህነት ማላቀቅና ማህበራዊ ፍትህ የሰፈነበት የመሬት ባለቤትነት ማስፈንና ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መብትን ወዘተ ማረጋገጥ ዓላማ ያደርጋል። የልማት ኮሙኒኬሽን የልማት ተግባራትን በማስተማር በማዝናናትና በማሳወቅ ስለ ልማት፤ ድህነትና ስራ አጥነትን በሚቀንሱ፤ መሀይምነትንና ኋላ ቀር አመለካከቶችና ዕሴቶችን ማስወገድ በሚቻልበት ሁኔታ አጀንዳ ቀርፆ ይሰራል። ይህን ተግባር በማከናወን ረገድ የሚዲያ ባለሙያዎችና የመንግስታት ግንኙነት የማይነጣጠሉ ሆነው ሊተገብሩት ገባል።

የልማት ዘገባ ዋና ተልዕኮው ልማት ከሀገሬው ህዝብ መዳፍ እንጅ ከሌላ ከየትም ሊመጣ እንደማይችል በማስገንዘብ የሀገሬውን ህዝብ ለልማትና መልካም አስተዳደር ስኬት እንዲነሳሳ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚን አስተሳሰብና ተግባርን እንዲፀየፍ ማነሳሳት የሚዲያው ስራ መሆን አለበት። ድህነትና ኋላ ቀርነትን መርታት የሚቻለው ኪራይ ሰብሳቢነትን መድፈቅ ሲቻል ነው። የአገራችን ፕሬስ በህግ የተሰጠውን ተልዕኮ መወጣት ካለበት በዚህ መንገድ ሊደገፍ ይገባዋል። የአገራችን ፕሬስ የልማትና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ወሳኝ ሚናውን ተወጣ የምንለውም አዲሲቱ ኢትዮጲያን በአዲሱ የፖለቲካ ዕሴትና ባህል መገንባት ሲችል ነው።